
የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

# የህፃናት መቆያ አገልግሎት
# መስጫ ማእከል
# ረቂቅ ማኑዋል



ጥር 2011

አዲስ አበባ

# መግቢያ

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እስትራቴጂክ ግብ በመቅረፅ በየደረጃ ባሉ ጽ/ቤቶች በማውረድና በመስራት ተግባሩን ትኩረት ሰጥቶበት እየገመገመ አቅጣጫ እያስቀመጠ ይገኛል፡፡ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባወጣው የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀፅ 48(6) በተሰጠው ስልጣን የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 36(1) "ሐ" መሠረት ህፃናት ከወላጆቻቸው ማግኘት የሚገባቸው እንክብካቤ እንዲያገኙ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ተቋማችንም ይህንን የህፃናት ማቆያ አገልግሎት መስጫ ማእከል ማቋቋሙ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ ረቂቅ ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1 . አጭር ርዕስ፦

ይህ ማኑዋል "የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የህፃናት ማቆያ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ማኑዋል/ ጋይድ ላይን ተብሎ ይጠቀሳል ፡፡

2. ትርጓሜ

2.1 "ማዕከል" ፡-ማለት የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ቅጥር ግቢ የሚገኝ ተቋሙ ሠራተኞች በስራ ሰዓት ህፃናት ልጆቻቸውን የሚያቆዩበት ሥፍራ ነው፡፡

2.2"ሕፃን ተንከባካቢ ወይም (ሞግዚት)"ማለት በኤጀንሲው የሠራተኞችን ሕጻናት ደህንነት በመጠበቅና አገልግሎት ለመስጠት የተቀጠሩ ባለሙያ ወይም ሠራተኛ ነው፡፡

2.3"ተገልጋይ"ማለት፡-በማዕከሉ ሕጻናት ልጆቻቸውን በማስገባት የእንካብካቤ ድጋፍ የሚሰጣቸው የኤጀንሲው ሰራተኛ የሆኑ ወላጆችና ልጆቻቸው ማለት ነው፡፡

2.4 "ሕፃን" ማለት ከሦሥት አመት በታች የሆነናየእናቱን ጡት የሚጠባ ወይም ከጡት ሌላ ወተት ምግብ ወዘተ የሚጠቀምና የቅርብ ክትትል እንካብካቤና ድጋፍ የሚያስፈልገው ልጅ ነው፡፡

2.5 "ጨቅላ ሕፃን" ማለት ወላጅ እናቱ የወሊድ ፍቃድዋን ከሚጠናቀቅበት አራተኛው ወር መጨረሻ ቀጥሎ ካለው ቀን አንስቶ እስከ 12 ወር ዕድሜ ያለው ልጅ ነው፡፡

2.6 "የሚውተረተር ሕፃን" ማለት ነገሮችን የማወቅ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ሁኔታው ከፍተኛ እድገት የሚያሳይበት ከ13 ወር እስከ 36 ወር እድሜ ያለው ልጅ ነው፡፡

2.7 " ሠራተኛ "ማለት በኤጀንሲው ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመቀጠር አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሰው ነው፡፡

2.8 "ኤጀንሲ /ተቋም/" ማለት በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፡፡

2.9 በዚህ ማንዋል በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

3.የማዕከሉ አስፈላጊነት፡-

የኤጀንሲው ሴት ሠራተኞች ከወሊድ በኋላ ወደ ስራ ገበታቸው በሚመለሱበት ወቅት ሕፃን ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉ የሚገባቸውን እንክብካቤና ጥበቃ እንዲያገኙ የሚደረግበት የሕፃናት ማቆያ ማዕከል በማቋቋም አገልግሎት መስጠት በማስፈልጉ ነው፡፡

## 4. የማዕከሉ ዋና ዓላማ

በኤጀንሲው የሚሰሩ ሠራተኞች ከወሊድ በኋላ ወደ ስራቸው በሚመለሱበት ወቅት ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ማዕከሉ በመምጣት ሕጻን ልጆቻውን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በማድረግ የሕፃናቱን ደህንነት ማስጠበቅና የሴቶችን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ነው፡፡

## 5 .የማዕከሉ ዝርዝር ዓላማ፡-

5.1 በተቋሙ የሚሰሩ ወላጆች በተለይ ሴት ሠራተኞች ከወሊድ በኋላ ወደ ስራ ገበታቸው በሚመለሱበት ወቅት ሕጻን ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉና እየተንከባከቡ መስራት እንዲችሉ ማድረግ፡

5.2 እናቶች/ወላጆች በልጆቻቸው ምክንያት ከስራ ገበታቸው እንዳይቀሩ በማስቻል በተመደቡበት የሥራ መስክ ያለምንም ሃሳብ ሙሉ ኃይላቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውንና ጊዜያቸውን ተጠቅመው ውጤታማ ሥራ እንዲያከናውኑ ማስቻል፤

5.3 ሕፃናት ከወላጅ እናታቸው ማግኘት የሚገባቸውን እንክብካቤና ጥበቃ እንዲያገኙ በማድረግ ህጻናት የተሟላ አካላዊና አእምሮአዊ እድገት እንዲኖራቸው ማድረግ፡

5.4 በሴት ሰራተኞች ላይ የሚደረሱ የስራና የሃሳብ ጫናዎችን በመቀነስ የውሳኔ ሰጪነት አመራር ሚናቸውን ማሳደግ፡፡

5.5 ሴት ሰራተኞች ለሌሎች የሕፃናት ማቆያዎች ይከፍሉ የነበረውን ክፍያ በማስቀረት የወጪ ስጋት መቀነስ፡

5.6 እናቶች ሕፃናቱን ጡት እንዲያጠቡ ለማበረታታ ነው፡

## 6. መቋቋም

ክፍሉ ወይም ቦታው በሕፃናቱ ጤናና አካል ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ኬሚካሎች፣ ብናኞች፣ ጨረሮችና ሽታ ነፃ የሆነና የራቀ ፣የድምጽ ብክለት የሌለበት፣ በቂ የፀሐይ ብርሃንና አየር ዝውውር ያለበት ለደህንነት ምቾት ሊሰጥ የሚችል ሥፍራ መሆን አለበት

## 7. የተፈፃሚነት ወሰን ፡-

7.1 በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ውስጥ በመስራት ላይ የሚገኙ ሴት ሠራተኞች እና በልዩ ምክንያት ኮሚቴው አይቶ ውሳኔ ሲሰጥ ወንድ ሰራተኛ ከ3 ዓመት በታች ባሉ ሕፃናት ልጆቻቸው ይሆናል፣

7.2 በማቆያው ተመድበው በሚሰሩ ሰራተኞች እና ለስልጠና ለስብሰባና ለተለያዩ የመንግስት ስራ ለማስፈፀም ከ3 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ይዘው ወደ ኤጀንሲ የሚመጡ የሪጅን፣ የቅ/ጽ/ቤትና የመስክ ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. የማዕከሉ ይዘት

### 2.1 ውስጣዊ ይዘትና ቁሳቁስ

ማዕከሉ ለሕጻናቱ እንደ እድሜ ደረጃቸው ከ4 ወር እስከ 12 ወራት ጨቅላ ህፃናት ፣ ከ13 ወር እስከ 36 ወር ለሚሆኑ ሕፃናት የተለያዩ ክፍሎችና በውስጡም የተለያዩ ቁሳቁሶችን የያዘ ሲሆን እንደሚሰጡት አገልግሎት የሚለያዩ ናቸው፡፡

2.2.1 የሚገኙ ቁሳቁሶች የሕፃናት አልጋና መቀመጫ ወንበር ፣ቴሌቭዥን ፣ፍሪጅ የምግብ ማሞቅያ ውሃ ማጣሪያ የተለያዩ የማረፊያ ፍራሾች ፣የመጸዳጃ እቃዎች የቁም ሳጥን የሕፃናት ገላ መታጠቢያ ፕላስቲክ የተለያዩ መጫወቻ አሻንጉሊቶች የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

### 2.2.2. በህጻናቱ ማቆያ አገልግሎት ውስጥ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው ፣

ሀ. የመኝታና የማረፊያ ቦታ፣

ለ . የመጫዎቻ ቦታ፣

ሐ የምግብ ማብሰያ ቦታ፣

መ. የመመገቢያ ቦታ፣

ሠ. የንጽህና መጠበቅያና የህጻናት የመጸዳጃ ቦታ፣

ረ. የእንክብካቤና የቅርብ ክትትል ቦታ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ

## 2.2.3.የመኝታ ክፍል፡-

2.2.3.1 ለተንከባካቢዎች እይታ አመቺ ሆኖ በተመሳሳይ ጊዜ የመኝታና የመጫወቻ ክፍሉ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆን አለበት፡

2.2.3.2 በቂ የተፈጥሮ ብርሃን የሚያገኝ፣ በጥላ የተጋረደና ቀጥታ የፀሐይ ጨረር የማያስገባ መሆን አለበት፡

2.2.3.3..የተመጣጠነ የሙቀት መጠን ንፁህ አየር ሊዘዋወርበት የሚያስችል በአንድ ክፍል ከ10 ያልበለጡ ጨቅላ ሕፃናት የሚይዝ መሆን አለበትአስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰው ሰራሽ የሙቀት መቆጣጠሪያ መጠቀም የሚችል መሆን አለበት፣በሕፃናት ቁጥር ልክ አልጋ፣ ፍራሽና የሕፃናት የተለያዩ የተንጠለጠሉ ቅርፃቅርፆች፣ የሙቀት መቆጣጠሪያ መሣሪያ መያዝ አለበት፣

2.2.3.6 የህፃናቱ አልጋ ስፋት ከ75 ሳ/ሜ በ135 ሳሜ ያልበለጠ የተንከባካቢ መተላለፊያ ከ90 ሳ/ሜ ያላነሰ በአልጋዎቹ መሀል የሚኖረው ስፋት ከ45 ሳ/ሜ ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 2.2.4 የመጫወቻ ክፍል

2.2.4.1 ጊዜያቸውን በጨዋታ የሚያሳልፉበት ክፍል በመሆኑ ደህንነቱ የተጠበቀና በህፃናቱ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ከሚችሉ ነገሮች የፀዳ መሆን ይኖርበታል፡፡

2.2.4.2. ተንከባካቢዎች በነፃነት ክትትል ሊያደርጉ የሚችሉበት አቀማመጡም ለህፃናቱ ደህንነትና ምቾት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል ፣ የመጫወቻ ክፍሉ ለህፃናቱ በቂ የመዘዋወሪያ ቦታ እንዲኖረው ይደረጋል፣

2.2.4.3. የመጫወቻ ክፍሉ ወለል ለስላሳና በግጭት ወቅት ጉዳት ሊያስከትል የማይቻል ምንጣፍ የተነጠፈ መሆን ይኖርበታል ፡

2.2.4.4 አዋቂዎች ወደ ህፃናቱ መጫወቻ ክፍሉ ከመግባባታቸው በፊት ንፅህናቸውን ስለመጠበቃቸውና ህፃናቱን ለበሽታ ከሚዳርጉ ነገሮች ስለመጠበቃቸው ማረጋገጥ አለባቸው፣

### I **ለጨቅላ ህፃናት** (infant stage) የሚዘጋጁ የሕፃናት መጫወቻ፣

ሀ. ለሕጻናቱ እይታን የሚስቡ፣አሻንጉሊቶችና ልዩ ልዩ መጫወቻ ቁሳቁስ ምቹና ግልጽ የሆኑ ክፍት ቦታ ላይ እንዲቀመጡ፣

ለ. ክፍሉ ግድግዳዎች የሀገርን ባህልና እሴት የሚያሳዩ ሆነው ሊዘጋጁ ይገባቸዋል፣

ሐ. ለመዳህና ለመቆም በሚሞክሩበት ጊዜ የሚደገፉባቸው ወንበር፣ ጠረጴዛዎች፣ ሼልፎች እንዳይንሸራተቱ ከግድግዳው የተያያዘ መሆን አለበት ፣

መ. አንድ መጫወቻ ክፍል ከ 10 የማይበልጡ ጨቅላ ሕጻናትን ለማስተናገድ እንዲቻል እና ለአንድ ሕጻን ነፃ የመጫወቻና መንቀሳቀሻ ቦታ 2.82 ካሬ ሜትር ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ።

### II ለሚውተረተር ህጻናት(toddler stage) የሚዘጋጁ መጫወቻዎች፣

ሀ. የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ጡንቻዎቻቸውን የሚያጠነክርና እንዲበረቱ እገዛ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፣

ለ. የመጫወቻ ቁሳቁስና አሻንጉሊቶች የሕፃናቱን እውቀትና የአእምሮ ደረጃ ሊያዳብር የሚችል በቀላሉ ሊያገኛቸው የሚችሉበት ቅርብና ግልጽ ቦታ ማስቀመጥ፣ ለመነካካትና ለመለማመድ እንዲሁም አካባቢያቸውን ለማወቅ የሚጠመዱበትና እረፍት አልባ እድሜ ላይ በመሆናቸው ይህን ሊረዳ የሚችል ሊሆን ይገባል፣

ሐ.. የክፍሉ ግድግዳዎች በመማሪያ ፊደላት በእንስሳትና በተለያዩ ስእሎች የተሞላና ትኩረት የሚስቡ መሆን አለባቸው፣

መ.. በአንድ የመጫወቻ ክፍል ከ 15 ያልበለጡ የሚውተረተሩ ሕጻናትን ማስተናገድ የሚችል 2.82 ካሬ ሜትር ስፋት ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፣

ሠ. ክፍሉ የመጫወቻ ቁሳቁስ ቴሌቪዥን፣ አሻንጉሊት፣ የሕጻናት ወንበርና ጠረጴዛ የፊደል ገበታ ለሕፃናቱ የተዘጋጀ ባህላዊ ስዕችና ቅርፃ ቅርፆች የያዘ መሆን አለበት፣

ረ..ከመጫወቻ ክፍል ውጭ መጫወት የሚፈልጉ ህፃናት ካጋጠሙ በመስሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ በማዕከሉ አጠገብ ሳይርቁ ቦታ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡

### 2.2.5 የንፅህና መጠበቂያ ክፍል

የንጽህና መጠበቂያ ክፍል በቂ አየር የሚዘዋወርበት ሆኖ ከቀጥታ ፀሃይ ጨረርና ንፋስ ከለላ ያለው መሆን አለበት፡፡ በዚህ ክፍል የእቃ መደርደሪያ፣ ሳጥን፣ የልብስ መቀየሪያ ጠረጴዛ፣ የህጻናት መታጠቢያ ገንዳ፣ የኤሌትሪክ ውሀ ማሞቂያ፣ የህጻናት መጸዳጃ ፖፖ፣ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት እና ሌሎች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 2.2.6 የምግብ ማዘጋጃና መመገቢያ ክፍል

2.2.6.1 ጡት የሚጠቡ ህጻናት እናቶቻቸው ለማጥባት በሚመጡበት ወቅት አረፍ ብለው ሊያጠቡ የሚችሉበት ቦታና ተጨማሪ ምግብ የሚጠቀሙ ህጻናት ምግባቸው በሚዘጋጅበትና ከተዘጋጀም በኂላ በወላጆች እናቶቻቸው ወይም በተንከባካቢያቸው የሚመገቡበት ነው

2.2.6..2 ክፍሉ በቂ የተፈጥሮ ብርሃን የሚገባበት ንጹህ አየር የሚዘዋወርበት ቀጥታ የጸሀይ ጨረር የማይገባበት ክፍል መሆን አለበት፤ የማብሰያ ክፍሉና መመገቢያው ተያያዥ ሆነው ህጻናቱ የማይደርሱበት የተከለለ መሆን አለበት።

2.2.6.3 ክፍሉ የምግብ ማብሰያ ምድጃ (የኤሌትሪክና ሲሊንደር)፣ ፍሪጅ፣ የውሀ ማጣሪያ፣ ማሞቂያ፣ የማብሰያና የመመገቢያ ቁሳቁሶች ማጠቢያ ቦታ (ሲንክ)፣ እቃ ማስቀመጫ መደርደሪያ ሳጥን ፣ የህጻናት መመገቢያ ጠረጴዛና ወንበር የያዘ የአዋቂ ወንበር የያዘ መሆን አለበት፣

# ክፍል ሶስት

## ለህጻናት ማቆያ የሚያስፈልግ የሰው ሀይልና የሚጠብቅ ስነ ምግባር

### 3.1 የሰው ሀይል

እንደሚስተናግዱ ሕጻናት ብዛትና የተቋሙ ስፋት አንጻር የሰው ሀይል ቁጥር የሚወሰን ሆኖ ፡

3.1.1 በሕጻናቱ አያያዝና እንክብካቤ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና 10+3 ያጠናቀቀች የሕጻናት ማቆያ ስልጠና የወሰደች የመጀመሪያ እርዳታ አስፈላጊውን ስልጠና የወሰደች በባህሪዋ፣ በጸባይና በስራዋ ምስጉን የሆነች፣

3.1.2. ተቋሙ ከ15 ሕፃን ቁጥር በላይ የሚያስተናግድ ከሆነ አንድ ነርስ ሊኖር ይገባል፡

3.1.3 አንድ ተንከባካቢ (ሞግዚት) 5 ሕጻናት መንከባከብ ሲኖርበት ከዚህ በላይ ሕፃናት የሚኖሩ ከሆነ ተጨማሪ ሞግዚት ያስፈልጋል፣

### 3.2 የህጻናት ማቆያው የስራ ሰዓት

3.2.1. የማቆያው አገልግሎት መስጫ ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ሆኖ ሰዓቱም በመንግስት የስራ ሰአት ከጠዋት 2.30 እስከ 11.30 ብቻ ይሆናል።

3.2.2 ከላይ የተጠቀሰው ሰዓት የምሳ ሰአትንም ይጨምራል፣

# ክፍል አራት

# ኃላፊነቶች

## 4.1 የሴቶች ህጻናተና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት

ሀ. በተቋሙ ውስጥ የህፃናት ማቆያ እንዲቋቋም የማድረግ፣
ለ. ቁሳቁሶችና የሰው ሀይል እንዲሟላ አስፈላጊው በጀት እንዲያዝ ማድረግና መነሻ ጥናቶችን የማቅረብ
ሐ. የህጻናት ማቆያው የአካባቢ ጸጥታና ንጽህና መጠበቁን የማረጋረጥ፣
መ. ማቆያውን በመወከል አስፈላጊ የሆኑ ስምምነቶችን ማከናወን፡፡

## 4.2 የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት

ሀ. በተፈቀደው መደብ ሞግዚት፣ ነርስ ፣የሙያና አካባቢደህንነት ባለሙያና ፅዳት ሰራተኛ በተፈቀደው መደብ መቅጠር ወይም መድቦ ማሰራት

ለ. የሠራተኞችን የስራ ሰዓት መውጫና መግቢያ ሰዓት መከታተል፡፡

ሐ. ሠራተኞቹ መታወቂያ ካርድ የማዘጋጀትና የመስጠት

## 4.3. የግዢ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊነት

ሀ. ለሕፃናት ማቆያ ማዕከል የሚያስፈልጉ ግብዓት ሲፈቀድ ማሟላት

ለ. ለተመደቡት ሠራተኞች ደመወዝ በየወሩ የመክፈል

## 4.4 በሕጻናት ማቆያው የሚመደቡ ሰራተኞች ኃላፊነትና ተጠያቂነት

4.4.1 ከተላላፊ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው ምርመራ እንዲያደርጉ ሲጠየቁ ለምርመራ የመቅረብ ወይም የምርመራ ውጤት የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው

4.4.2 የተቀጠሩ ሰራተኞች ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት በህጻናት ማቆያው ውስጥ ባለ ሕጻን ላይ ጉዳት ካደረሱ፣ የወንጀልና የፍታሀ ብሄር ኃላፊነት አለባቸው፣

4.4.3 ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ 3.3.2 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ማንዋል ውጪ የሚሰሩ ከሆነ በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

4.4.4 የሕጻናቱ ደህንነት ስለመጠበቁ በሳምንቱ መጨረሻ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ የዳይሬክቶሬት ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፣

4.4.5 በዚህ ምንዋል ክፍል 4.3 የተመለከቱትን አሰራሮች የማክበር ግዴታ አለባቸው

## 4.5 የሕጻናት ማቆያ ተገልጋዮች ኃላፊነት

4.5.1. በዚህ መመሪያ ማቆያው የተፈቀደላት ሴት የመንግስት ሠራተኛ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆነች፤አገልግሎቱ ለማግኘት ሕጻን ልጇን ማስመዝገብ አለባት፣

4.5.1 ለመመዝገብ የሕጻን ልጇን የልደት የምስክር ወረቀት ተገቢውን ክትባት መውሰዷን / መውሰዱ/ የሚገልጽ የሀኪም ማስረጃ ማቅረብ አለባት፣

4.5.3 የመንግስት ሰራተኛዋ የራስዋ እና የሕፃንዋን (የሕፃኑን) ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ የማቅረብና በዚሁ አገልግሎት የሚውል መታወቂያ የመውሰድ ግዴታ አለበት፣

## 4.6 የሕጻናቱ ማቆያ ተገልጋዮች ግዴታ

4.6.1 በዚህ ማንዋል መሠረት የተቋሙን አሰራሮች የማክበር፣

4.6.2 ጠዋት 2፡30 ሕጻናትን ይዘው የመምጣትና ለተንከባካቢ የማስረከብ በመውጫ 11፡30 ሰአትም የተሰጣቸው ልዩ መታወቂያ ይዘው ሕጻኑን ፈርሞ የመረከብ ግዴታ አለባቸው፣

4.6.3 ጠዋት ከ4፡00-4፡15 ከምሳ በኃላ 9፡00-9፡15 ሕፃን ለማጥባት፣ ለመመገብና ለማየት እንደሚችሉ ሆኖ ከተፈቀደው ሰዓት ውጪ በስራ ገበታቸው ላይ መገኘት እንዳለባቸው ፣

4.6.4 ለየእለቱ ለሕፃኑ የሚያስፈልገው በቂ የተመጣጠነ ጤናማና የአስተሻሸግ ስርአቱን በጠበቀ መልኩ የታሸገ /የተያዘ ምግብ ከመመገቢያ ቁሳቁስ ጋር ለተንከባካቢዎች የማስረከብ፣

4.6.5 ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የምግብ አይነት ከሆነ በበቂ የምግብ አይነት ዝርዝርና የአዘገጃጀት ማብራሪያ ጽሁፍ ጋር አያይዞ የማቅረብ፣

4.6.6 ለእለቱ የአየር ሁኔታ የሚስማማ ለ1 ቀን የሚበቃ ንጹህ ቅያሪ ልብስ ጫማና ካልሲ አንሶላና ብርድ ልብስ እንዲሁም የቆሸሹና የተቀየሩ ልብሶችን መያዣ የሚሆን ቦርሳ ከረጢት የማቅረብ፣

4.6.7 ሕጻናቱ ሲመጡ ንጽህናቸውን ጠብቀውና የታጠቡ ልብሶችን አልብሰው የማስረከብና ለቀኑ የሚያገለግል በቂ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አዘጋጅተው የማቅረብ፣

4.6.8 አገልግሎቱን ፈልገው የሚመጡ ወላጆችና ሕጻናት ለተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡ አለመሆናቸውን የማረጋገጥ፣

4.6.9 ሕጻናቱ በእድሜያቸው የሚሰጠውን ክትባትና የጉበት በሽታ መከላከያ ክትባት መውሰዳቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ ሀላፊነት አለባቸው፡፡

## 4.7. የሕጻናት ማቆያ የአሰራር ስርአት

4.6.10 ወላጆች አገልግሎት ከማግኘታቸው በፊት መመዝገብ ፣

4.6.11 የሕጻኑ ወላጅ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ከተቋሙ የተዘጋጀ ልዩ መታወቂያ ካርድ ለአገልጋይዋ ወይም ለሞግዚቷ ሰራተኛ የመስጠት፣

4.6.12 የሚሰጠው መታወቂያ የእናትየዋና፣ የሕጻኗ/ኑ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት መሆን አለበት፣

4.6.13 ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስረከብ በሚመጡበት ወቅት ልዩ የመታወቂያ ካርድ ይዘው በመቅረብ አስመዝግበው ማስረከብ ሲረከቡ መረከባቸውን በፊርማ ማረጋገጥ አለባቸው፣

4.6.14 ሕፃኑ የታመመ ትኩሳት ያለበት ሌላ ችግር ያለበት ከሆነ አስቀድሞ ሐኪም ቤት የመውሰድና የማሳከም

4.6.15 ሕፃኑ መታመሙ በማዕከሉ ባለሙያ ሲገለጽ ወዲያው ወደ ሕክምና/ሆስፒታል ወይም ሌላ የሕካምና ተቋም/የመውሰድ

4.6.16 መድሃኒት የሚወስድ ሕፃን ካለ ስለመድሃኒቱ አሰጣጥ ሰዓቱን የሚያስፈልገው መጠን ለሞግዚቶች አስቀድሞ ማሳወቅና ማስመዝገብ

4.6.17 መታወቂያ የያዘ ወላጅ በማይገኝበት ወቅት ሁለተኛ ወላጅ፣ አባት ወይም አሳዳጊ ማንነትን የሚገልጽ ከህጋዊ የመንግስት አካል የተሰጠው የራሱ መታወቂያ ካርድ እና ተቋሙ የተሰጣቸው ልዩ መታወቂያ ካርድ አያይዘው በማቅረብ ልጃቸውን መውሰድና ስለመውሰዳቸው በፊርማ ማረጋገጥ፣

4.6.18 ከተቋሙ ሰራተኛ ውጪ የሕጻናት ማቆያውን አገልግሎት ለማግኘት በተቋሙ ለተለያዩ ስብሰባ፣. ስልጠናና መሰል ፕሮግራሞች አገልግሎት ፈልገው በሚመጡበት ወቅት ህጋዊ የሆነ ማንነታቸው የሚገልጽ የመታወቂያ ካርድ ይዘው መቅረብ አለባቸው፣

4.6.19 በጊዜያዊነት አገልግሎቱን ፈልገው የመጡ በመሆኑም ልጆቻቸውን ሕጻናት ማቆያው ለማቆየት ይዘው በሚመጡበት ወቅት ሕጻኑ ክትባት የወሰደበትና ከተላላፊ በሽታ ነፃ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፡ በመታወቂያ ካርዳቸው አማካኝነት ምዝገባ እንዲከናወንና ለልጃቸውም ልዩ መለያ(ኮድ) እንዲሰጥ ተደርጎ ለወላጆቻቸው መሰጠት አለበት፡፡ ለህጻኑ የሚያስፈልጉ አልባሳትና ምግብ ማቅረብም ይኖርባቸዋል፡፡

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

### 5.1 .ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕጻናትን በተመለከተ

ወደ ሕፃናት ማቆያ ማዕከሉ የአካል ጉዳት ወይም ልዩ ፍላጎት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ተገቢ ድጋፍና እንክብካቤ የሚሰጥበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

### 5.2. በጀት

ለሕፃናት ማቆያ ማዕከሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ለማዕከሉ ሠራተኞች ደመወዝ ሥራ ማስኬጃ የሚያስፈልግ ወጪዎች በየዓመቱ በኤጀንሲው በጀት የሸፈናል፡፡

### 5.3 . የክትትልና የቁጥጥር ስርአት

5.3.1 የሕጻናት ማቆያ ማእከል አገልግሎት ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥብቅ ክትትል የሚጠይቅ አገልግሎት በመሆኑ በተቋሙ የስራ አካባቢና ደህንነት ባለሙያ ወይም የሰው ሀብት አስተዳደር በሚመደበው ባለሙያ በሳምንት አንድ ቀን የአገልግሎቶች ጥራት፣ የአካባቢውና የሕጻናቱ ንጽህና በአግባቡ መጠበቁን፣ በሕጻናት ላይ ጥቃት እንዳይደርስ ፣ የሕጻናት ጤናና ሌሎች በማእከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ጥብቅና ተከታታይ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለተቋሙ ሪፖርት ይደርጋል፡፡

5.3.2.የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በዚህ ማንዋል አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 5.5 መሠረት ከተመረጡ የኮሚቴ አባላት ጋር በየጊዜው የማእከሉን ይዘት፣ አገልግሎት አሰጣጥ የቁሳቁስ አቅርቦት የአካባቢው ደህንነት ላይ የመገምገም የመከታተልና የመደገፍ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ቢያንስ በወር 2 ጊዜ በአካል በማእከሉ በመገኘት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

### 5.4 ወደ ሕፃናት ማቆያው እንዲገቡ የተፈቀደላቸው

በሕፃናቱ ማቆያ አገልግሎት የሚጠቀሙና አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞች፣ የስራ አካባቢና ደህንነት ባለሙያ ወይም የሰው ሀብት ባለሙያ፣ የኮሚቴ አባላትና የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ባለሙያዎች በስተቀር ወደ ማእከሉ መግባት እንደማይቻልና ለጉብኝት ከመግባታቸው በፊት በሚመለከተው አካል ፍቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

## 5.5 የኮሚቴ አባላት ፣

1. የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት --- ሰብሳቢ
2. የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ---- አባል
3. የግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ---- አባል
4. የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ---- አባል
5. የስነ ምግባር ዳይሬክቶሬት ---- አባል

## 5.6. የኮሚቴው አባላት ኃላፊነት

- የኮሚቴው አባላት የማእከሉን የውስጥ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡

--እንደ አስፈላጊነቱ የአሰራር ማሻሻያዎች ያደርጋል፡፡-

- የማዕከሉን ተግባር የመቆጣጠርና የመደገፍ

- በማዕከሉን አጠቃቀም ላይ የሚወሰኑ ጉዳዮች የመወሰን ኃላፊነት አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ ይህ ማንዋል የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የህፃናት ማቆያ ማዕከል የአሰራር ማንዋል ከ-------- 2011 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ይውላል፡፡